EFDA
የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY

ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የመድኃኒት እደላና የምክር አገልግሎት ለአግባባዊ የመድኃኒት አጠቃቀም

ባሳለፍነው ሳምንት እትማቸውን በኢትዮጵያ አግባባዊ የመድኃኒት አጠቃቀም ውስንነት በስፋት እንደሚስተዋልና ችግሩም ከባለሙያው የመድሃኒት አስተዛዘዝ ጀምሮ እድላና ተጠቃሚው ድረስ እንደሚዘልቅ በመጠቆም፣ ለመፍትሄው ሊደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄና ትኩረት ይዘን መቅረባችን ይታወሳል። በዛሬው እትማችንም ከባለፈው በመቀጠል በተለይ በመድኃኒት እደላ ሂደት ከባለሙያዎች የሚጠበቁ የተለያዩ ተግባራትና ጥንቃቄ የሚፈልጉ ጉዳዮችን እንቃኛለን።

## 1.የመድኃኒት እደላ ሂደት

በመድኃኒት እደላ ሂደት በተለይ ለታካሚው የታዘዘለት መድኃኒት ትክክለኛነቱን ከማረጋገጥ ጀምሮ በአግባቡ የማሰራጨት ተግባር ላይ አስፈላጊውን መረጃና የምክር አገልግሎት በመስጠትና በሚታዘዝበት ወቅትም ሆነ በአጠቃቀም ላይ የሚከሰቱ ስህተቶች እንዲስተካከሉ ወይም እንዲቀንሱ ለማድረግ የመድኃኒት ባለሙያዎች ወሳኝ ሚና አላቸው። በእደላው ሂደት ውስጥ የተለያዩ ተግባራቶች ይከናወናሉ። ይህም ስራ የተለያዩ ሂደቶች አሉት።

### 1.1. መድኃኒቱን ለማደል ማዘጋጀት

የመድኃኒት ባለሙያው ከላይ ያየናቸውን መረጃዎች ሕጋዊነት እና ትክክለኛነት ካረጋገጠ በኋላ የታዘዙትን መድሃኒቶች በጥንቃቄ በመምረጥ ማዘጋጀትና ተገቢ በሆነ ማሸጊያ ውስጥ ማስገባት ይጠበቅበታል።

### 2.4 ስለሚታደለው መድኃኒት መረጃዎችን በማሸጊያው ላይ ማስፈር

ቀጣዩ በመድኃኒት እደላ ወቀት የሚተኮርበት የታካሚው ስም፣ የመድሀኒት አቀማመጥ፣ የመድሀኒቱ የጽንስ ስም፣ የመድኃኒቱ ጥንካሬና መጠን እንዲሁም አወሳሰድ በማሸጊያው ላይ በትክክል መፃፍ ነው።

### 2.5 መረጃና ምክር

በማስከተል ያለው አንኳር ጉዳይ የታካሚውን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት መድኃኒቶችን እንዴት እንደሚጠቀም አስፈላጊ መረጃና ትዕዛዝ እንዲሁም የምክር አገልግሎት መስጠት ነው። ይህ ማለትም ታካሚው የሚወስደው የመድኃኒት መጠን በቀን ምን ያህል ጊዜ፣ በስንት ሰዓት ልዩነት፣ እንዴት መውሰድ እንዳለበት/ከምግብ በኋላ፣ ከምግብ በፊት ወይስ ከምግብ ጋር/፣ መቼ መውሰድ እንዳለበት፣ ለምን ያህል ቀናት መውሰድ እንዳለበት፣ እንዴት እንደሚወሰድ/በመዋጥ፣ በማኘክ፣ በፊንጢጣ.....ወዘተ/የመድኃኒቶች አቀማመጥ እና ሊያውቋቸው ስለሚገቡ የመድኃኒቶች የጎንዮሽ ጉዳቶች በሚመለከት ታካሚው በቀላሉ በሚረዳውና ግልፅ በሆነ ቋንቋ በቃልም በፅሁፍም ሊሰጠው ይገባል።

ታካሚውም ቢሆን በመድኃኒት ባለሙያው የሚሰጡ የምክር አገልግሎቶችን በንቃት መከታተል፣ ያልገባውን መጠየቅ እና ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል። ስለሆነም በማንኛውም የሕክምና ተቋም ለመታከምም ሆነ መድኃኒት ለመግዛት በሚሄዱበት ጊዜ የባለሙያዎችን ሰዓት ያለአግባብ አባክናለሁ ብለው ስለሕክምናዎ ሁኔታ ያልገባዎትን መረጃ ከመጠየቅ ወደ ኋላ ማለት ተገቢ አይደለም።

ባለሙያው ከላይ የዘረዘርናቸውን ግዴታዎች መወጣት እንዳለበት ሁሉ ታካሚውም በተለያዩ ምክንያቶች በዕደላ ስህተት ምክንያት የሚመጡ ችግሮችን ለመቀነስ በማንኛውም የሕክምና ተቋም ባለሙያዎች መድኃኒት ሲሰጡ ከላይ የተገለፁ የምክር አገልግሎቶች በመድኃኒት ባለሙያው ካልተገለፁ አስታውሶ መጠየቅ ይኖርብዎታል።

ከዚህ አንፃር ማንኛውንም ከዚህ በፊት የወሰዱትን ወይም በመውሰድ ላይ ያሉትን፤ በባለሙያ ትዕዛዝ ወይም ያለባለሙያ ትዕዛዝ የተገዙ መድኃኒቶችን፣ የባሕል መድኃኒቶችን ስም እንዲሁም የዝግጅት አይነትና የሚወሰደውን መጠን በዝርዝር መዝግበው በመያዝና ለባለሙያዎች በማሳየት ለሀኪምዎ ተጨማሪ መረጃ በመስጠት በመድኃኒት መደራረብ ምክንያት የሚመጣን ችግር መቀነስ ወይም ማስወገድ ይቻላል። ምን አልባት ስለመድኃኒትዎ አወሳሰድ እና ሌሎች መረጃዎችን በትክክል መረዳት የሚያስቸግርዎ ከሆነ ቤተሰብ ወይም ጓደኛ አብሮዎት እንዲሄድ ማድረግ ተገቢ ነው።

### 2.6 የመድኃኒት ማዘዣውን መመዝገብ እና ፋይል ማድረግ

በመጨረሻም በመድኃኒት እደላ ጊዜ ባለሙያው የመድኃኒት ማዘዣውን መመዝገብ እና ፋይል ማድረግ አለበት። ተቋማት የመድኃኒት አጠቃቀማቸውን ለማወቅ፣ ለሚመለከተው አካል ወቅታዊ ሪፖርት ለመላክ፣ ፍላጎትን ለመተንበይና በቀጣይ የሚያስፈልገውን በጀት ለመወሰን እንዲሁም ሀብትን በአግባቡ ለመጠቀም ከታካሚው የተሰጠውን ማዘዣ መዝግቦ መያዝ እና በቀኑ ቅደም ተከተል ፋይል ማድረግ ይጠበቅበታል። በመጨረሻም በህጉ መሰረት የማስወገድ ስራ ሊሰራ ይገባል።

የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒቶች ማዘዣ ወረቀቶች ፋይል ሆነው መቀመጥ ያለባቸው ቢያንስ እስከ 5 ዓመት ሲሆን ከእነዚህ ውጭ ያሉ መድኃኒቶች ደግሞ እስከ 2 ዓመት እንዲቆዩ ከተደረጉ በኋላ በአግባቡ እንዲወገዱ ማድረግ ይጠበቃል።

የመድኃኒት ባለሙያው ተገቢ የሆነ ስነምግባር ሊኖረው ይገባል። በተለይ የመድኃኒት ባለሙያ ከታካሚው ጋር የሚያደርገው የመረጃ ልውውጥ በትሕትና የመናገር፣ የመድኃኒት አዳይ ባለሙያ ስለሚሰጠው መረጃ ትክክለኛነት ሙሉ እምነት እንዳለው ማሳየት፣ ግዴለሽ አለመሆን ይልቁንስ በትኩረት እየተከታተለው ለመሆኑ የምልከት መግባቢያ ቋንቋዎችን መጠቀም፣ አላስፈላጊ የሆኑ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የሚያመዝኑና ብዥታ የሚከቱ ንግግሮችን ማስወገድ ይጠበቅበታል።

### ማጠቃለያ

በአጠቃላይ ትክክለኛ የመድኃኒት እደላ ታካሚው በአግባቡ ከመድኃኒቱ ማግኘት የሚገባውን ጥቅም እንዲያገኝ ለማድረግ፣ የመድኃኒቱን የጎንዮሽ ጉዳቶች ለመቀነስ፣ የሕክምናው ጥራት ለማሻሻል፣ መድኃኒቶችም ያለአግባብ እንዳይባክኑ ለማድረግና ፍትሀዊ ላልሆነ የገንዘብ ወጪ እንዳይዳረጉ ያግዛል።

የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒት እና የጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን የሕክምና አገልግሎት ጥራት ለማሻሻልና ትክክለኛ የመድኃኒት እደላ እንዲኖር ለማድረግ የተዘጋጀው ግንቦት 2012 ተሻሽሎ የወጣው መመሪያ ኢትዮጵያን ጨምሮ በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ትክክለኛ ያልሆነ የመድኃኒት እደላ የተለመደ አሰራር እንደሆነ ያስረዳል።

በመልማት ላይ በሚገኙ ሀገሮች ዙሪያ ከሚታዩ ትክክለኛ ያልሆነ የመድሃኒት እደላዎች መካከል የታዘዘው መድኃኒት በትክክል አለማንበብ፣ በሀኪም ትዕዛዝ የሚሰጡ መድኃኒቶችን ያለማዘዣ ወረቀት ማደል፣ ለታካሚው አስፈላጊ የሆነ የቃልና የጽሁፍ የመድኃኒት መረጃ እና ተገቢውን የምክር አገልግሎት አለመስጠት፣ በዋጋ ውድ የሆኑ መድሃኒቶችን ማዘዝ እና የማዘዣ ወረቀቱ የተሟላ አለመሆን ተጠቃሾች ናቸው።

በመሆኑም ከታዘዘልን መድኃኒት የሚጠበቀውን ጥቅም ለማግኘትና ጉዳትን ለመከላከል ብሎም ለአግባባዊ የመድኃኒት አጠቃቀም በአግባባዊ የመድኃኒት እደላ የተካተተውን ትክክለኛ የመድኃኒት መረጃና ምክርን መቀበልና መተግበር በእጅጉ አስፈላጊ መሆኑን በአጽንዖት እናስገነዝባለን።

Tel : +251-11-552-41-22
+251-11-552-41-22
P.o.box. 5681
Free call. 8482
http://www.fmhaca.gov.et/contact/
E-mail contactefda@efda.gov.et
Telegram channel link
https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ